ከሐምሌ 2008 - መስከረም 2009 ዓ.ም.    ቅፅ 2፣ እትም 3

# ስሙኝ

## በዚህ እትም:


- ሴማልማ በAWID ዓለም ዓቀፍ ጉባዔ
- ሁለት የሴማልማ የረጅም ጊዜ ነዋሪዎች ከዩኒቨርሲቲ ተመረቁ
- ከመጠለያም በላይ: የሴማልማን ስራ የሚዘግብ ዕትም
- አስገድዶ የደፈረው የ15 ዓመት እስራት ተበየነበት
- አቅምን ያገናዘበ የህፃናት ማቆያ አስፈላጊ ነው


## ሴማልማ በብራዚል የAWID ዓለም ዓቀፋዊ ጉባዔ ላይ ተሳተፈ

በAssociation for Women's Rights in Development (AWID) ጋባዥነት ሴማልማ በ13ተኛው ዓለም ዓቀፍ ጉባዔ ላይ ከጳጉሜ 3፣ 2008 - መስከረም 1፣ 2009 በብራዚል ተሳተፈ።

ይህ ዓለም ዓቀፋዊ ከፍተኛ ስብሰባ በየሶስት ወይም አራት ዓመቱ ይካሄዳል። በዚህም ዓመት ከዓለም ዙሪያ የተሰባሰቡ ከ2000 በላይ የሴቶች ማህበራት መሪዎች፣ ለጋሽ ድርጅቶች፣ የልማትና በቀጥታ ከሴቶች ጋር የሚሰሩ ድርጅቶች እና የሴት መብት ተከራካሪዎች ተሳትፈዋል።



ማሪያ ሙኒር፣ የሴማልማ ሥራ አስፈፃሚ ከUN Women ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፉምዚሌ ሚያምቦ-ንጉካ ጋር በጉባዔው

የዚህ ዓመት የጉባዔው መወያያ ርዕስ ‘ለሴቶች መብትና ፍትህ የጋራ ሃይልን መገንባት’ የሚል ነበር።

የሴማልማ ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክትር እና የኦሮሚያ ፕሮጀክት አስተባባሪ በስብሰባው ተሳትፈዋል። በተለያዩ ርዕሶች ላይ በተዘጋጁ ስብሰባዎች ላይ ተሳትፈው የሴማልማንም ልምድ ለሌሎች አካፍለዋል። በተጨማሪም ከሌሎች ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ድርጅቶች ጋር የልምድ ልውውጥ አድረገዋል።

## ሁለት የሴማልማ የረጅም ጊዜ ነዋሪዎች ከዩኒቨርሲቲ ተመረቁ

የሴማልማ የረጅም ጊዜ ነዋሪ የሆኑት ቃልኪዳን ጌጡ እና ቤዛዊት ገበየሁ ባለፈው ዓመት መጨረሻ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀዋል፡ ፡

የ23 ዓመት ወጣት የሆነችው ቃልኪዳን ወደ ማረፊያው ስትመጣ የ14 ዓመት ልጅ ነበረች። ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ በገበያ ጥናት የሙያ ዘርፍ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቃ በተማረችበት ሙያ ወደ ስራ ተሰማርታለች። ከ5 ዓመት በፊት ሴማልማ የመጣችው የ23 ዓመቷ ወጣት ቤዛ ደግሞ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በሴማልማ የአዲስ አበባ ማረፊያ እየኖረች ተከታትላለች። ከኮተቤ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ተምርቃም ወደ ስራ ተሰማርታለች።

ሁለቱም ተመራቂዎች  በሶስት ዓመት የዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ወቅት የኪስ ገንዘብ እና ለአስፈላጊ የትምርት ወጪዎች ከሴማልማ ድጋፍ ሲደረግላቸው ቆይቷል። በእረፍት ጊዜያቸው ሁለቱም በበጎ ፈቃደኝነት በሴማልማ ቢሮ እና በማረፊያ ቤቶቹ ከሰራተኞች ጋር በመሆን የስራ ልምምድና ነዋሪዎችን የመርዳት በጎ አድራጎት ስራ ሲሰሩ ቆይተዋል። በተለይም ታማሚዎችን በማስታመምና አራስ እናቶችን ሲያግዙ ቆይተዋል።

በምርቃት ፕሮግራማቸው ላይ የሴማልማ ሰራተኞች በጎንደርና በአዲስ አበባ ተገኝተው የደስታቸው ተካፋይ ሆነዋል።




ተመራቂዎቹ በማረፊያው በተዘጋጀላቸው ድግስ ላይ



ቃልኪዳን ከሴማልማ ሰራተኞችና ሌሎች ጋር

## ደረጃቸውን የጠበቁ የማሰልጠኛ ማንዋሎች ተዘጋጁ

ሴማልማ ለሚያደርጋቸው የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ደረጃቸውን የጠበቁ የማሰልጠኛ ማንዋሎች አዘጋጅቷል። በስልጠና እና አቅም ግንባታ ፕሮገራም ሴማልማ ፖሊሶችን፣ ዓቃቤ ህጎችን፣ የማህበረሰብ አባላትን እና ትምህርት ቤቶችን አቅም ለማጎልበት የተለያዩ ስልጠናዎችን ይሰጣል።

ቀደም ሲል ስልጠናው በተለያዩ አሰልጣኞች በተዘጋጁ ማሰልጠኛ ማንዋሎች በመጠቀም የሚሰጥ ሲሆን ማህበሩ ደረጃውን የጠበቀ ወጥ የማሰልጠኛ ማንዋል በፖሊስ ኮሌጅ ምምህርና በሌሎች ባለሙያዎች እንዲዘጋጁ አድረጓል።

ማንዋሎቹ በሴማልማ ሰራተኞች፣ባለድርሻ አካላትና የማህበሩ ቦርድ አባላት ግምገማ በማድርግ በአዲስ አበባ ፕሮጀክቶች ወደ ስልጠና ተገብቷል።

በቀጣይነት ኦሮሚያ ፕሮጀክትም ማንዋሎቹን የአስልጣኞች ስልጠና በመስጠት ለመጠቀም አቅዷል።


## ተመላሽ ስደተኞችን ለመርዳት የሴማልማ እና የIOM በጋራ መስራት

ሴማልማ ከIOM ጋር በመሆን በብዛት ከሳዑዲ አረቢያ የሚመለሱ ሴቶችን መልሶ የማቋቋም ሥራ ሰርቷል።

በስደት በሚኖሩበት አገር መቆየት የማይፈልጉ ወይም የማይችሉ እና ወደ ሃገራቸው መመለስ የሚፈልጉ ሴቶችን ድጋፍ ለመስጠት ከIOM ጋር በመተባበር በመስከረም 2016 የሴማልማ የኦሮሚያ መጠለያ 30 ከአዲስአበባ ወደ ኦሮሚያ የሄዱ ተመላሽ ስደተኞችን እና 20 በሴማልማ ማረፊያ ቤት ነዋሪ የሆኑ የህገወጥ የሰው ዝውውር ተጠቂዎችን የመደገፍ ስራ ሰርቷል። ፕሮጀክቱ የክህሎት ስልጠናና መልሶ የማቋቋም ድጋፍ ከመስጠቱ በተጨማሪ ገቢ ማግኛ ስራዎቻቸውንም ይደግፋል።

ከዚህ ቀደም ሴማልማ በ2013 ድንገተኛ የሳዑዲ አረቢያ ተመላሽ ኢትዮጵያውያንን በቦሌ ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማረፊያና በከፈተው ተጨማሪ ማረፊያ ቤት ከUN Women እና NPA ጋር በመሆን ለተመላሽ ስደተኞች ተገቢውን ድጋፍ አድርጎአል።

## ‘ከመጠለያም በላይ’: ሴማልማን የተመለከተ ዕትም




የዕትሙ የፊት ገፅ

የሴማልማ ዋነኛ ለጋሽ ከሆኑት አንዱ ውማን ካይንድ የተባለው ድርጅት በሐምሌ 2016 የሴማልማ ስራዎችን በተመለከተ የተጠናከረ ዘገባ አዘጋጅቷል። ‘ከመጠለያም በላይ’ ተብሎ የተሰየመው ባለ 44 ገፅ ዘገባ በኢትዮጵያ እና በዚምቧቤ ሁለመናዊ መጠለያ የሚሰጡትን የሁለት ሴቶች ድርጅቶችን ስራ ይዘግባል።

የፀሃፊዎች፣ ጥናት አጥኚዎች እና ፎቶ የሚያነሱ ሰዎች ቡድኑ በኢትዮጲያ የቢሮ እና የመስክ ሥራዎችን በመስራት ከሴማልማ አመራር አካላት ፣ ባለ ድርሻ አካላት እና ከነዋሪዎች ጋር ለመነጋገር ጊዜ ወስደዋል። ዘገባው የሴማልማን ስራዎች፣ የደረሰበትን ስኬት እና የገጠሙትን ችግሮች ይዳስሳል። በአዲስ አበባ በተደረ ገዝግጅት የተመረቀው ዕትም ሴማልማ ለሴቶች እየሰጠ ስላለው አገልግሎት እንደ ዋንኛ የመረጃ ምንጭ ያገለግላል።

ዘገባው ዘገባው በሚፃፍበት ወቅት የተነሱ ጥራት ያላቸው ፎቶ ግራፎች በእንግሊዙ ብሄራዊ ጋዜጣ ዘ ጋርዲያን ላይ የፎቶ ታሪክ ለመፃፍ አገልግሏል።

በፎቶ የተደገፈውን ታሪክ ለማየት የሚከተለውን ይመልከቱ: https://www.theguardian.com/global-development/gallery/2016/jul/27/ethiopia-women-girls-safe-houses-shelter-ethiopia-female-survivors-violence-in-pictures)

# ታዳጊዋን የደፈረው የ15 ዓመት ቅጣት ተበየነበት

**ኦሮሚያ ኢትዮጵያ፡** የ14 ዓመቷ ማርታ (ስሟ ተቀይሯል) የሚኤሶ አውራጃ ፍርድ ቤት ዳኛ ለገሰ ጌታነህ ላይ የ15 ዓመት  እስራት ሲበይኑበት ሰምታ ምንም እንኳን በዚህ ችግር ውስጥ በማለፏ ብትከፋም፤ በመጨረሻ ፍርድ በመሰጠቱ ተደስታለች።

ከአንድ አመት በፊት ነበረ የእንጀራ አባቷ እናቷ ለቀብር ሄዳ ሳለ አስግድዶ የደፈራት። “ከተናገርኩኝ እኔን እና እናቴን እንደሚገለን ሸጉጥ እያወናጨፈ አስፈራራኝ” ትላለች። ማርታ ፈርታ ስለ ነበር እናቷ እና አክስቷ እርጉዝ መሆኗን እስካወቁበት ቀን ድረስ ይህንን መጥፎ አጋጣሚ ከሁሉም ደብቃ ነበር። ቤተሰቦቿ ጉዳዩን ለፖሊስ ሲያመለክቱ ፖሊስ ተጨማሪ እርዳታ እንድታገኝ ወደ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ መርቷቸው ከመኖሪያ አካባቢዋ የ3 ሰዓት ርቀት ላይ ወደሚገኘው ወደ አዳማ መጠለያ እንድትገባ ተደረገ። ይህም የሆነው በመጠለያ ውስጥ የቅድመ-ወሊድ የጤና ክትትል እና የህጉን ጉዳይ በአግባቡ መከታተል እንድትችል ነው።

ከማርታ ጋር በግል እና በቡድን ክፍለ ጊዜ የምትሰራው አማካሪዋ ህይወት አደራ “ማርታ ወደ ሴማልማ ስትመጣ ብቸኛ ነበረች” ትላለች። “ሁል ጊዜ ታለቅሳለች፣ ተስፋ ቆርጣለች እንዲሁም ስለ ተሸከመችው ልጅ ምን እንደምታደርግ እርግጠኛ አልነበረችም። በአስተሳሰቧም በአዕምሮዋም በጣም ተጎድታ ነበር። በመጠለያው በተደረገላት የምክር አገልግሎት እና እራስን የማብቃት ስልጠናዎች አማካኝነት ማርታ ከድብቷ ወጥታ ልጇን መቀበል እና መውደድን ለምዳለች። እንዲሁም ከሌሎች ጋር መግባባት እና አዳዲስ ሰዎችን መቀበል ጀምራለች። በፍርዱ በጣም ተደስታለች። እናቷ ጋር ተመልሳ ትምርቷን ካቆመችበት ከስድስተኛ ክፍል መቀጠል ትፈልጋለች” ትላለች አማካሪዋ።



ሴማልማ የኦሮሚያ ማረፊያ

የሴማልማ የአዲስ አበባው ፕሮጀክት UNFPA, NPA, Comic Relief, WOMANKIND, Ethiopiaid UK and Ireland የሚደገፍ ሲሆን የኦሮሚያው  እና የአዳማው ፕሮጀክት ደግሞ  በUN Women ይደገፋል ።  ማረፊያ ቤቱ ከጥቃት የሚያገግሙ ሴቶች እና ህፃናት መጠለያ ፣ምግብ፣ ምክር፣ ጤና አገልግሎት እና የክህሎት ማሳደግያ ስልጠናዎች በተጨማሪ ለነዋሪዎች በጣም አስፈላጊ የሆነውን የህግ ክትትል አገልግሎት ይሰጣል። ይህ ደግሞ ተጠቂዎች በራሳቸው ጉዳይ ዋንኛ ምስክሮች እንዲሆኑ በማዘጋጀት፣ የፍርድ ቤት ቀጠሯቸውን በመከታተል እና ወደ ፍርድ ቤት ፣ ሀኪም ቤት እና ፖሊስ ጣቢያ ሲሄዱ እና ሲመጡ አብሯቸው በመሆን ተጠቂዎች ስለጉዳያቸውን እንዲመሰክሩና እና ወንጀለኞች ላይ ክስ እንዲመሰርቱ ያግዛል።

በተጨማሪም ሴማልማ ማህበረሰቡን ፣ ፖሊስ፣ የሃይማኖት መሪዎች ፣ የእድር መሪዎችና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን አካላት የሚደግፉ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይሰራል። ለፖሊሶች በሚሰጠው ስልጠና ምክንያት ፖሊሶች በሴቶች እና በህፃናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን የሚቀበሉበት እና የሚያነጋግሩበት መንገድ ልዩ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው የተሻለ ግንዛቤ አዳብረዋል። የሴማልማ ስራ ፍትህ በተሻለ ሁኔታ እንዲሰፍን አድርጓል።

**“ብናገር እኔና እናቴን እንደሚገድለን ሽጉጡን እያወናጨፈ አስፈራራኝ።”**

ቅፅ 2፣ እትም 3

የዚህን መፅሄት ቅጂ
በኢሜይል ለማግኘት
info@awsad.org ላይ
መልዕክት ይላኩ

የሴቶች ማረፊያና ልማት ማህበር (ሴማልማ) ዋንኛ ለጋሾቻችንን ማመስገን ይፈልጋል:

- **NPA**
- **የኔዘርላንድስ ኤምባሲ በUNFPA በኩል**
- **አይሪሽ ኤይድ እና የዳኒሽ ቆንስላ በኢትዮጵያ በUN Women በኩል**
- **ውማን ካይንድ ወርልድ ዋይድ**
- **ኮሚክ ሪሊፍ**
- **ኢትዮጵያኤድ (ዩኬ፣አይርላንድ)**

የሴቶች ማረፊያና ልማት ማህበር (ሴማልማ) በኢትዮጲያ የሚገኝ በጎ አድራጎት ማህበር ሲሆን የተቋቋመውም የሴቶችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን የላቀ ለማድረግ እና አካላዊ እና ስነ ልቦናዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች እና ታዳጊ ሴት ልጆች ድጋፍ ለመስጠት ነው። ሴማልማ በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

በማረፊያ ቤቱ ሴማልማ ስነልቦናዊ ድጋፍ፣ ጊዜያዊ መጠለያ፣ ምግብ፣ የህክምና አገልግሎት እና መሰረታዊ ትምህርት እና ክህሎቶችን የሚያዳብሩ ስልጠናዎችን ለተጠቃሚዎች ይሰጣል። ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ሴማልማ ከአራት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሴቶች እና ህፃናት ድጋፍ ሰጥቷል። ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች፣ ፖሊስ ፣ የሴቶች እና የህፃናት ጉዳይ ቢሮ እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የአቅም ግንባታ ስልጠናም ይሰጣል።

የሴቶች ማረፊያና ልማት
ማህበር

ስልክ: +251 116672290
ፋክስ: +251 116625461
ኢሜይል: awsad950@gmail.com

# አቅምን ያገናዘበ የህፃናት ማቆያ አስፈላጊ ነው

በማሪያ ሙኒር፣ የሴማልማ ዋና ስራ አስፈፃሚ

የማህብሩ መሪ ሆኜ በምሰራበት ስራዬ ሁለት አይነት ሴቶችን አያለሁ። እናቶች የሆኑ እና ያልሆኑ። እናትነት በህይወት ከሚያጋጥሙ ምርጥ እና አስደሳች ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው። ለድሃ እናቶች ግን እናትነት ደስታም ትልቅ ፈተናም ይሆንባቸዋል። ትንንሽ ልጆች ያሏቸው እናቶች ስራ እንዳይሰሩ እና ቤት ውስጥ እንዲቀመጡ የሚያደርጋቸው ዋንኛ ምክንያት በመሆኑ።

የመዋዕለ ህፃናት ወይም የህፃናት ማቆ ያ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ቁጥር እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ቁጥራቸው እየጨመረ ቢሆንም የግል በመሆናቸው ለድሃ እናቶች በጣም ውድ ናቸው። በመንግስት የሚተዳደሩ መዋዕለ ህፃናት ደግሞ ቁጥራቸው በጣም አናሳ ነው። ስለዚህ ድሃ እናቶች ልጆቻቸው ዕድሜያቸው ለትምህርት እስኪደርስ ቤት ሆነው ማሳደግ ግዴታቸው ይሆናል።

አንዳንድ ጊዜ እናቶች ልጆቻቸውን ይዘው መሄድ የሚችሉባቸውን መደበኛ ያልሆኑ ስራዎችን ይሰራሉ።


በ2013 ነዋሪዎች እና የበፊት ነዋሪዎች ስራ ሲሄዱ ልጆቻቸውን ትተው ሊሄዱባቸው የሚችሉባቸው ነፃ የህፃናት ማቆያ አገልግሎት በአዳማ ጀምረናል። ይህ ወዲያውኑ ለብዙ ሴቶች አዲስ በርን ከፍቶላቸዋል ምክንያቱም በተለያዩ የስራ መስኮች ትንሽ ንግድ መጀመር ወይም ተቀጥሮ መስራትን በመሳሰሉ ስራዎች እንዲሳተፉ እና ከጥገኝነት እንዲላቀቁ አድርጓል። ስለዚህ ነፃ ወይም አቅምን ያገናዘቡ ህፃናት ማቆያ ለማህበረሰባችን በተለይም ለሴቶች እራሳቸው በመቻል በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል።



የቀድሞ ሴማልማ ነዋሪዋ ትዕግስት በቀን ስራዋ



ልጆች በሴማልማ የህፃናት ማቆያ



ትዕግስት ከስራ በኋላ ከልጇ ጋር ስትገናኝ